IBO

IB DIPLOMA PROGRAMME
PROGRAMME DU DIPLÔME DU BI
PROGRAMA DEL DIPLOMA DEL BI

M04/166/S(1)

**AMHARIC A1 – STANDARD LEVEL – PAPER 1**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU MOYEN – ÉPREUVE 1**
**AMHARE A1 – NIVEL MEDIO – PRUEBA 1**

Monday 10 May 2004 (afternoon)
Lundi 10 mai 2004 (après-midi)
Lunes 10 de mayo de 2004 (tarde)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a commentary on one passage only. It is not compulsory for you to respond directly to the guiding questions provided. However, you may use them if you wish.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Rédigez un commentaire sur un seul des passages. Le commentaire ne doit pas nécessairement répondre aux questions d'orientation fournies. Vous pouvez toutefois les utiliser si vous le désirez.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un comentario sobre un solo fragmento. No es obligatorio responder directamente a las preguntas que se ofrecen a modo de guía. Sin embargo, puede usarlas si lo desea.

ከሚከተሉት ምንባቦች አንዱን መርጠህ አስተያየትህን ስጥ(ስጪ)።

**1. (ሀ)**

## አይቀርልኝ ነገር (1992)

ፈረንጅ አገር ሄጄ፣
ስራውን ለምጄ፣
ብገባ ብወጣ፣
ስልጣኔ ጣጣ።
ከሰው ጋር እየዋልኩ ብተኛ ብነሳ፣
ብቸኝነት በዛ ደግሞ ልቤ ሳሳ።
ፈገግታ ጫጫታ ዘር ማንዘሩ ጠፍቶ፣
በሮቦት ተመርቶ፣ ምርቱ ተርፎ ሞልቶ፣
እኮምፒውተር ጋር ሁሉ ተጎልቶ፣
ለእግዜር ሠላምታ ጊዜውን ቆጥቦ፣
እንዴት ይዘለቃል ሰው ፍቅርን ተርቦ?
በአንድ ጣሪያ ስር ኑሮን እየገፉ፣
የሰው ልጅ ተለየ መገናኘት ጠፋ።
ቪድዮ ቴሌቪዥን ብቻ የሰው ተስፋ፣
ብሎ የሚጣጣር ብቸኝነት ይጥፋ።
እጅግ ብቸኝነት አብሮ እየዋሉ፣
ይሄ ስልጣኔ ምንድን ይሆን ውሉ?
በአካል የማወጋው፣ በአካል የሚያወጋኝ፣
ናፈቀኝ፣ ናፈቀኝ፣
ናፈቀኝ፣ የሰው መልክ፣
ሰላም! የሚለኝ ሰው፣ ሳቁ ብሎ ትርክክ።
እንዴት ነሽ? እንዴት ነህ? የምለው ወገኔ፣
ናፈቀኝ ያ ለዛ ይምጣልኝ ከጎኔ።
አብሮ መብላት፣
ማውጋት፣
መጓዝ ተያይዞ፣
ሃዘንን ደስታን በጋራ ተጋግዞ፣
ያቺ ትንሽ ጎጆ አመድ የነዛባት፣
ከፍቅር በስተቀር ምንም የሌለባት፣
የሰው ጓዝ የከብቱ፣ ትንፋሽ የበዛባት፣
ናፈቀችኝ እሷ፣
መች ሰውን ተካልኝ የአለም ትርምሷ?
ስልጣኔ ቅርሷ።
በኢንተርኔት ገዝቶ በኢንተርኔት ሸጦ፣
ሳይወርድ ሳይወጣ እቤቱ ተቀምጦ፣
እድገቱ ገስግሶ ስልጣኔ ቢንር፣
መች ሰውን ተካልኝ፣
ይህን ታላቅ ፍጡር።
አዬ ጉድ! መራራቅ አብረው እየዋሉ፣
ኧረ! ስልጣኔ ምንድን ይሆን ውሉ?
የቀረበው ርቆ፣ የራቀውም ቀርቧል፣
ገንዘብና ጊዜ እጅግ ተቆጥቧል፣
ሰው ተጠቀመ፣ ስልጣኔ መጥቋል
እኔን አልጠበቀም ዓለም ገስገሰ
ጊዜው መአበል ነው የልቤ አልደረሰ
የራሱን ገንብቶ የኔን አፈረሰ

እኛን ሳያማክር ዓለም ተለውጦ፣
እንኳንስ ተኝተን መች ሆነ ተሩጦ።
ፉክክሩ ከፍቶ አይኖቹን አፍጥጦ፣
አደርስበት ይሆን እግሬ ተንፈራግጦ?
በዚህ ቴክኖሎጂ ዘመን መረጃ፣
በኔ ኅታታነት መጠቀሚን እንጃ።
ዓለም ገሰገሰ እኔ ቢለኝም ቅር፣
ወደድኩም ጠላሁም አይቀርልኝ ነገር።

መሉ ሰለሞን፡ ጊዜ፡ 1994::

—የግጥሙ ዋና ጭብጥ ምንድነው?

—በግጥሙ ውስጥ የምእራቡ አለም ሕይወት እንደምን ቀርብዋል?

—ገጣሚዋ በአንባቢው አመለካከት ላይ ተጽእኖ ለማሳደር የተጠቀመችባቸው ቴክኒኮች ላይ አስተያየት ስጥ::

—ስለግጥሙ ያለህ አጠቃላይ አስተያየት ምንድነው?

# ኑሮ ካሉት!

ሳባ ዘነበ ተፈራ

ለሥራ ፈላጊዎች የወጣውን ማስታወቂያ አይቶ ለመመዝገብ የተኮለኮለው ወጣት እጅግ በጣም ብዙ ነበር:: እኔም ዛሬ ከወትሮው ዘግየት ብዬ ነበርና ከስፍራው የደረስኩት ጠጋ ብዬ አንዷን ወጣት "ይቅርታ እመቤት ምን አዲስ ነገር አለ ? ዛሬም እንደትናንቱ ነገ ይሉን ይሆን?" ስል ጠየቅኳት :: ወጣቷም ተስፋና ቅሬታ በተቀላቀለበት አንደበት "እንጃ ዛሬ እንኳን ተስፋ ያለው ይመስላል ፣ አንድ ሰው በዚህ በምታይው መስኮት በኩል ብቅ ብለው በኋላ ለሥራ ችግር እንዳትፈጥሩ ሰልፋችሁን በስርዓት ያዙ ብለው ነበር፣ በኋላ ሃሣባቸውን ካለቀየሩ" አለችኝ :: እኔም ከብዙ ፈተና በኋላ ቢገኝ ተብሎ ተስፋ የቋጠረለት ሥራ አሁን ያኘሁት ያህል ደስ አለኝ:: ከዛሬ ጋ ለአምስተኛ ጊዜ መመላለሴ አስመርሮኛል :: ወዲያውኑ ከዚያም ከተኮለኮለው ወጣት መሀል ሁለት ወጠምሻዎች እጃቸውን እያጨበጨቡ መጡ "በሉእ ኀበዝ ቦታችንን እንያዝ ምናልባት ዛሬ እንኳን ቢከትቡን፣ በሉእ! እንግዲህ እንዳመጣጣችን ሳይሆን እንደአቋቋማችን እንሰለፍ" አለ አንዱ ድምጹን ከፍ አድርጎ:: እኛም የመስሪያ ቤቱን አጥር ተደግፈን ሠልፋችንን ያዝን::

የፀሃይዋ ሙቀት እየጨመረ መጣ፣ ሰዓቱም እየረፈደ፣ ግን ምንም አዲስ ነገር አልነበረም:: ዛሬም መቆሙ እጅጉን ሠልችቶኝ ስለበር ከዚያው ከአጥሩ አካባቢ ጉሊት ደርድራ ትሸጥ ከነበረች አንዲት ሴት አጠገብ ካለው ድንጋይ ላይ ቁጭ አልኩኝ :: የገሮን ጥላዋን ከለላ ፈልጌ ነበርና ወደእርሷ ጠጋ ለማለት ስሞክር "አይዞሽ ጠጋ በይ ፣ ነይ ወዲህ ፣ ተቃጠልሽ እንደው ፣ ምንም መፍትሄ አልሠጧችሁም ? አሄሄ አይዞሽ ነይ ወዲህ" አለች :: "አይ ግድ የለም ይበቃል "አልኳት :: "አይ ልጄ ይህች ፀሐይ እንደሆነች እንደዘንድሮ ሠው ሆኗል አመሏ ተንኮል ሸር ለምዳለች ፣ ኋላ እንደእኔ ጠባብሳ እንዳትጥልሽ "አለችኝ :: በዙሪያዋ የተኮለኮሉት ህፃናት ቀልቤን ሰርቀውት ስለነበር ከልብ አላዳመጥኳትም ነበርና "የት ሄድሽ ልጄ ?ኧረ ተይ አታስቢ ልጄ ፣ በሐሳብ ምን ይገፋል ብለሽ? በማሰብ ቢሆንማ ኖሮ ዛሬ እኔ እንኳን ለራሴ ለአገር እተርፍ ነበር :: "ብላ ሳትጨርስ "እነዚህ ሁሉ ልጆችሽ ናቸው ?"አልኳት :: "አዎ የእኔው ናቸው :: "አለችኝ ፣ ከጀርባዋ ላይ ያለውን ሕፃን አውርዳ ለማጥባት እየሞከረች :: "እኮ ስድስቱም ?" አልኳት በመገረም ወደእርሷ እያየሁ :: "አዎ ልጄ ፣ምነው በዙብሽ ?"

አለችኝ ። "አይ መብዛታቸው ሳይሆን እድሜያቸው በጣም ተቀራራቢ ስለመሰለኝ ነው "አልኳት ። "አዎ በአናት በአናት ነው የወለድኳቸው " አለችኝ ። "በሉ ያዙ" እያለች እዚያው በተኮለኮሉበት ዳቦውን አደለቻቸው ። እርስ በርስ እየተያዩ ዳቦውን አዩት ።

ለእህል ያላነሱ ለስራ ያልደረሱ ሕፃናት ዙሪያዋ ተኮልኩለው በዚያች ሥራ ተብዬ ተቀምሶ ማደሩ ውስጤን ረበሸው ። "ለምን ብዙ ወለድሽ "አልኳት "ምን ይደረግ ብለሽ ነው ፣ ብልጡ፡ የለ እውቀቱ፡ ፣ እንዳው ሆድ ሞልቶ ማደር ብቻ ፣ '

ሳባ ዘነበ ተፈራ፡ እጣ፡ ሜጋ ማተሚያ ቤት፡ **1995**::

– ደራሲዋ ልታስተላልፍ የፈለገችው መልእክት ምን ይመስልሀል?

– የሁለቱን ዋና ገፀባህሪያት አቀራረብና አላማ አብራራ::

– የአጭር ልቦለዱ መቼት ገፀባህሪያቱን በማሳየት ረገድ ያለውን አስተዋፅዎ ግለፅ::

– የአጭር ልቦለዱ ፈገግ የሚያደርግ አቀራረብ በአንባቢው ላይ የሚያሳድረው ተፅእኖ ምንድነው?